# የዘመን ባንክ አ.ማ

## የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምልመላ እና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ

2018 ዓ.ም.

# ማውጫ


መግቢያ፣---3

ክፍል አንድ ---4

አጠቃላይ ጉዳዮች---4

1. አጭር ርዕስ፣ ---4

2. ትርጓሜ፣ ---4

ክፍል ሁለት---5

የተለያዩ ክፍሎች ሀላፊነት---5

3. የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት፣ ---5

4. የቦርድ ተግባርና ኃላፊነት፣ ---5

5. የኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣ ---6

6. የማህበሩ ፀሀፊ ተግባርና ሀላፊነት ---6

ክፍል ሶስት --- 6

የቦርድ አባላት ስብጥር፣ ብዛት፣ የአገልግሎት ዘመን እና መስፈርቶች --- 6

7. የቦርድ አባላት ብዛት እና የአገልግሎት ዘመን እና ዝቅተኛ መመዘኛ መስፈርቶች ---6

8. የቦርድ አባል ሆኖ ለመመረጥ የሚያስፈልጉ ዝቅተኛ የመመዘኛ መስፈርቶች ---7

**ክፍል አራት** ---10

**የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ማቋቋም፣ አባልነት፣ መመዘኛ እና ስብጥር** ---10

9. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ማቋቋም፣--- 10

10. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባልነት መመዘኛ እና ስብጥር --- 10

ክፍል አምስት --- 11

የእጩዎች ጥቆማ እና የምልመላ ሂደት --- 11

11. እጩዎችን በምድብ ማስቀመጥ--- 11

12. የእጩዎች ብዛት --- 12

13. የጥቆማ አቀባበል፡--- 12

14. እጩዎችን መመልመል --- 12

15. የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ምልመላ ሂደት--- 13

ክፍል ስድስት --- 13

የምርጫ አፈጻጸም --- 13

16. እጩዎችን ማሳወቅ እና የድምጽ አሰጣጥን መግለጽ--- 13

17. የድምጽ መስጫ ካርድ፣ --- 13

18. የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት፣ ---------------------------------------------------------------- 14
19. የምርጫው ውጤት ስለመግለጽ ---------------------------------------------------------- 15
20. የምርጫ ሰነዶችን ስለመያዝ ----------------------------------------------------------- 15
ክፍል ሰባት------------------------------------------------------------------------------ 15
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች--------------------------------------------------------------------- 15
21. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት፣ ------------------------------------------------------------ 15
22. መመሪያውን ስለማሻሻል፣ -------------------------------------------------------------- 15
23. የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች ---------------------------------------- 15
24. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ፣ ------------------------------------------------------------ 16
የማረጋገጫ ቅጽ------------------------------------------------------------------------- 17

# የዘመን ባንክ አ.ማ

# የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምልመላ እና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ

## መግቢያ፣

የኮርፖሬት መልካም አስተዳደር የባንኩን ባለአክሲዮኖች እና ሌሎች የባለድርሻ አካላትን ዘላቂ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችል ዋነኛ መሳሪያ ነው፡፡ የኮርፖሬት መልካም አስተዳደርን እውን ለማድረግ ከሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ውስጥ ትልቁን ሚና የሚጫወተው ደግሞ የተለያዩ ክህሎቶችን፣ ልምዶች እና የትምህርት ዝግጅቶችን ከጠንካራ ስነ-ምግባር ጋር አዋህዶ  የያዘ ነጻ እና ገለልተኛ የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲኖር ሲደረግ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሁሉንም ባለአክሲዮኖችን አሳታፊነት የሚያረጋግጥ፣ ግልጽ ሂደትን የሚያስቀምጥ እና የላቀ-ውጤት ማስመዝገብ የሚችሉ ብቃት እና ሥነ-ምግባር ያላቸውን ግለሰቦች የቦርድ አባል እንዲሆኑ አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥር የአሰራር መመሪያ ያስፈልጋል፡ ፡

እንዲሁም፣ ባንኩ ታህሳስ 2012 ዓ.ም ያወጣው "የዘመን ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ መመሪያ"ን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ካወጣቸው የባንክ የመልካም አስተዳደር መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 እና በባንክ ውስጥ ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ አካላት ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን ከሚደነግገው  መመሪያ ቁጥር SBB/89/2024 ጋር መጣጣም አለበት፡፡

በመሆኑም፣ የቦርድ አባላት ሊኖራቸው የሚገባን የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድ፣ ሥነ-ምግባር እና መሰል መስፈርቶችን የሚደነግግ፣ ጊዜያዊ የምልመላ እና አስመራጭ ኮሜቴ የሚቋቋምበትን ሁኔታ የሚያስቀምጥ፣ ለቦርድ አባልነት የጥቆማ፣ የምልመላ እና የምርጫ ሂደቱን የሚደነግግ ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የባንክ መልካም አስተዳደር መመሪያ ቁ. SBB/91/2024 አንቀጽ 9.1 ላይ በተደነገገው መሰረት በዘመን ባንክ አ.ማ የባለአክሲዮኖች መደበኛ 17ኛ ጠቅላላ ጉባዔ ፀድቆ ሊወጣ ችሏል፡፡

# ክፍል አንድ
# አጠቃላይ ጉዳዮች

## 1. አጭር ርዕስ፣

ይህ *መመሪያ* **"የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምልመላ እና የምርጫ አሠራር** ***መመሪያ*** (2018)" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ፣

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ *መመሪያ* ውስጥ፣

2.1. "**ባንኩ**" ማለት ዘመን ባንክ አ.ማ ነው፡፡

2.2. **"ቦርድ"** ማለት የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡

2.3. **"ዳይሬክተር"** ማለት የባንኩ ቦርድ አባል ነው፡፡

2.4. **"ሠራተኛ"** ማለት የባንኩን የዕለት ተዕለት ሥራዎች እንዲያካሂድ የተሾመ ወይም የተቀጠረ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው ነው፡፡

2.5. **"ጠቅላላ ጉባዔው"** ማለት የባንኩ ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ነው፡፡

2.6. **"ገለልተኛ ዳይሬክተር"** ማለት በባንኩ በማንኛውም አስተዳደር ውስጥ የማይሳተፍ፣ የቦርድ አባል ሆኖ የቦርድ አባልን ነጻ እና ሚዛናዊ አተያየት ከሚያዛባ ማንኛውም አይነት ውስጣዊ፣ ውጫዊ፣ የፖለቲካና ሌሎችም ተፅዕኖዎች ነጻ የሆነ፣ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ባለአክሲዮን ያልሆነ፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም የባንኩ ሠራተኛ ያልሆነ ወይም ከእነዚህ ጋር የመጀመሪያ ደረጃ የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና የሌለው፣ ከባንኩ ጋር ማንኛውም አይነት የውል ግዴታ ባለው ድርጅት ውስጥ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚ ያልሆነ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በፍርድ ቤትም ሆነ ከፍርድ ቤት ውጪ ባሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች ማንኛውንም አይነት የህግ ክርክሮች በባንኩ፣ በባንኩ እናት ድርጅት ወይም በባንኩ ተቀጽላዎች ላይ ያላቀረበ፣ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከባንኩ ጋር ማንኛውንም የቢዝነስ፣ የንግድ እና ሙያዊ ግንኙነቶች ያላደረገ፣ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የመልካም አስተዳደር መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀጽ 2.9 መሰረት የተቀመጠውን መስፈርት ሙሉ ለሙሉ የሚያሟላ ማለት ነው ፡፡

2.7. **"ተጽዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮን"** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከባንኩ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል 2% (ሁለት በመቶ) ወይም ከዚያ በላይ የአክሲዮን ድርሻ ያለው ሰው ነው፡፡

2.8. **"ተጽዕኖ ፈጣሪ ያልሆነ ባለአክሲዮን"** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከባንኩ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ውስጥ ከ2% (ሁለት በመቶ) በታች የአክሲዮን ድርሻ ያለው ሰው ነው፡

2.9. **"ኮሚቴ ወይም ኮሚቴው"** ማለት በባንኩ ጠቅላላ ጉባዔ የሚቋቋም ጊዜያዊ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ነው፡፡

2.10. **"ብሔራዊ ባንክ"** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፡፡

2.11. **"የፋይናንስ ተቋም"** ማለት ባንክ፣ መድን ሰጪ ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ ኩባንያ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ አነስተኛ መድን ሰጪ ኩባንያ፣ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ፣ የክፍያ ስርአት አንቀሳቃሽ፣ የካፒታል እቃ ፋይናንስ ኩባንያ፣ የሀዋላ ድርጅት፣ የውጭ ባንክ እንደራሴ ቢሮ፣ የፖስታ ገንዘብ አስተላላፊ ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን እና ፍቃድ የሚሰጠው ሌላ ተመሳሳይ ተቋም ነው፡፡

2.12. **በወንድ ጾታ የተገለፀው ለሴትም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡**

## ክፍል ሁለት
## የተለያዩ ክፍሎች ኃላፊነት

### 3. የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት፣

3.1. የባንኩን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምልመላ እና የምርጫ አሰራር ደንብና የአፈጻጸም መመሪያ ያጸድቃል፡፡

3.2. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል ፡፡

3.3. ለቦርድ አባልነት ይጠቁማል፣ ከተጠቆሙት ውስጥ ድምጽ በመስጠት ይመርጣል፡፡

### 4. የቦርድ ተግባርና ኃላፊነት፣

4.1. የባንኩ የቦርድ አባላት ጥቆማና የምርጫ ሂደት አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እንዲሁም በዚህ የአሰራር ደንብና የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት እንዲከናወን ያመቻቻል፤

4.2. ለጠቅላላ ጉባዔው በሚቀርበው አጀንዳ ውስጥ የኮሜቴ  ምርጫ ተካቶ እንዲቀርብ ያደርጋል፣

4.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ የምልመላና እና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ በማርቀቅ እንዲጸድቅ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤

4.4. ቦርዱ **"ኖሚኔሽን እና ሪሙኔሬሽን ኮሚቴ"** የተመለመሉ ገለልተኛ ዳይሬክተሮችን ስም ዝርዝር ከአስፈላጊው ማስረጃ ጋር ለኮሚቴው ያቀርባል፡፡

4.5. የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በክፍል 3 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

4.6. ለቦርድ ምርጫ የሚያስፈልጉ የድምጽ ካርዶች፣ የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ወይም የኤሌክትሮኒክስ የድምጽ መስጫ ሲስተም በአግባቡ ስለመዘጋጀቱ ያረጋግጣል፡፡

## 5. የኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

5.1. የቦርድ ዳይሬክተሮችን የምልመላ እና ምርጫ ሙሉ ሂደት ያስፈጽማል፣

5.2. የቦርድ አባላት ምልመላ እና ምርጫ ግልጽ፣ ፍትሀዊ እና ታማኝ በሆነ ሁኔታ እና አግባብነት ያለው የሀገሪቱ ህግ፣ የብሔራዊ ባንክ መመሪያ እና ይህን ሥነ-ሥርዐት በሚደነግጉት ህጎች መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

5.3. የአስመራጭ ኮሚቴው የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ታሽገው በማኅበሩ ጸሐፊ ቢሮ እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡

5.4. የአስመራጭ ኮሚቴው ቃለ-ጉባኤዎች በማኅበሩ ጸሐፊ ቢሮ እንዲቀመጡ ያደረጋል፡፡

## 6. የማህበሩ ፀሀፊ ተግባርና ኃላፊነት

6.1. የአክሲዮን ማህበሩ ጸሀፊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከመደረጉ አንድ ወር በፊት የቦርድ አባላት አስመራጭ ኮሚቴ እና የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለሚመረጡበት መስፈርቶች የሚገልጽ መግለጫ በአገሪቷ ሰፊ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች፣ በባንኩ በይነ መረብ እንዲሁም በሌሎች የኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች ለባለአክሲዮኖች እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡

6.2. የጠቅላላ ጉባኤው ቃለ ጉባኤ በብሔራዊ ባንክ እንዲጸድቅ አስፈላጊውን ሁሉ ያከናውናል፡፡

6.3. የአስመራጭ ኮሚቴው ቃለ-ጉባኤ እና የድምጽ መስጫ ሳጥኖች በማኅበሩ ጸሐፊ ቢሮ በተገቢው ሁኔታ እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>የቦርድ አባላት ስብጥር፣ ብዛት፣ የአገልግሎት ዘመን እና መስፈርቶች</u>

## 7. <u>የቦርድ አባላት ብዛት፣ የአገልግሎት ዘመን እና ዝቅተኛ መመዘኛ መስፈርቶች</u>

7.1. ቦርዱ በባንኩ መመስረቻ ፅሑፍ ላይ የተቀመጠው የዳይሬክተሮች ብዛት ይኖረዋል፡፡

7.2. የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል፡-

ሀ) ከጠቅላላው የቦርድ አባላት መቀመጫዎች ውስጥ 1/3ኛ የሚሆኑት ተጽእኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ የተመለመሉና የተመረጡ ፤

ለ) ከጠቅላላው የቦርድ አባላት መቀመጫዎች ውስጥ 1/3ኛ የሚሆኑት በሁሉም ባለአክስዮኖች የተመለመሉና የተመረጡ ፤ እና

ሐ) ከጠቅላላው የቦርድ አባላት መቀመጫዎች ውስጥ 1/3ኛ የሚሆኑት ገለልተኛ ዳይሬክተሮች የሆኑ በቦርድ የተመለመሉ እና በሁሉም ባለአክስዮኖች የተመረጡ ሊሆኑ ይገባል።

መ) የጾታ ስብጥርን ለመጠበቅ ቢያንስ ሁለቱ የቦርድ አባላት ሴት መሆን አለባቸው።

ሠ) ከሁለት ያልበለጡ የባንኩ ሰራተኞች የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሊሆኑ ይችላሉ።

ረ) በተቻለ መጠን ቦርዱ በሚከተሉት የሙያ ዘርፎች ላይ የትምህርት ዝግጅት እና ተጨባጭ ልምድ ያላቸው ዳይሬክተሮች እንዲኖሩት ማድረግ ይገባል። እነሱም፡- በንግድ ስራ አመራር፤ በባንክ እና/ወይም በፋይናንስ፣ በአካውንቲንግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ፣ በንግድ አስተዳደር፣ በኦዲቲንግ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኢንቨስትመንት አስተዳደር ናቸው።

ሰ) በባንኩ ውስጥ ተጽእኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮን ከሌለ ሁሉም ዳይሬክተሮች በሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚመረጡ ይሆናል።

7.3. አንድ ተመራጭ ዳይሬክተር በተከታታይ ከስድስት አመታት በላይ ዳይሬክተር ሆኖ ሊመረጥ አይችልም ። ነገር ግን የባንኩ የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በቦርዱ ውስጥ ቀጣይነት እንዲኖር እና አንዳንድ ነባር የቦርድ አባላትን በድጋሚ እንዲመርጥ ከፈለገ እነዚህን ዳይሬክተሮች ለአንድ ተጨማሪ ጊዜ ብቻ ሊመርጥ ይችላል። በዚህ ሁኔታ በድጋሚ የተመረጡ የቦርድ አባላት ቁጥር ቢበዛ ከባንኩ የቦርድ መቀመጫዎች አንድ ሶስተኛ (1/3) በላይ ሊሆን አይችልም።

## 8. የቦርድ አባል ሆኖ ለመመረጥ የሚያስፈልጉ ዝቅተኛ የመመዘኛ መስፈርቶች፤

በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ላይ የተቀመጡት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ለቦርድ አባልነት የሚጠቆሙ ግለሰቦች ከታች የተቀመጡትን የእውቀት፣ ልምድ እና ብቃት፣ የታማኝነት፣ የፋይናንስ ጤናማነት፣ ከጥቅም ግጭት ነጻ የመሆን፣ የመወሰን ነጻነት እና ግዜ የመስጠት መመዘኛዎችን ሊያሟሉ ይገባል።

### 8.1. የእውቀት፣ ልምድ እና ብቃት መመዘኛ

8.1.1. ገለልተኛ ያልሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ለመሆን የሚጠቆመው ግለሰብ በዕውቀት፣ ልምድ እና ብቃት ደረጃ ቢያንስ የሚከተለውን ሊያሟላ ይገባል፡-

8.1.1.1. ከታወቀ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያለው መሆን አለበት፤

8.1.1.2. በንግድ ስራ አመራር፤ በባንክ እና/ወይም በፋይናንስ፣ በአካውንቲንግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ፣ በንግድ አስተዳደር፣ በኦዲቲንግ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኢንቨስትመንት አስተዳደር ቢያንስ የሰባት (7) ዓመታት ልምድ ያለው መሆን አለበት፤

8.1.1.3. በማንኛውም የፋይናንስ ተቋም የቦርድ አባልነት የማያገለግል መሆን አለበት፡፡

8.1.2. ለገለልተኛ ዳይሬክተርነት የሚጠቆመው ግለሰብ በዕውቀት፣ ልምድ እና ብቃት ደረጃ ቢያንስ የሚከተለውን ሊያሟላ ይገባል፡-

8.1.2.1. በባንክ ሙያ፣ በሒሳብ አያያዝ፣ በፋይናንስ፣ በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በህግ፣ በቴክኖሎጂ እና ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች ውስጥ በአንዱ ከታወቀ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የማስተርስ ዲግሪ ወይም በተመጣጣኝ ሙያዊ ብቃት ያለው፤ እና

8.1.2.2. በፋይናንስ ዘርፍ ወይም ከፋይናንስ ዘርፉ ጋር በተገናኘ በማስተማር/በማማከር ወይም በኦዲት ወይም በስጋት አስተዳደር ወይም በማናቸውም ሌላ ተዛማጅነት ባላቸው መስኮች ቢያንስ (10) ዓመታት የሙያ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

## 8.2. የባህሪ እና የስነ-ምግባር መመዘኛ

8.2.1. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው የሚጠቆሙ ግለሰቦች ተዓማኒ፣ መልካም ስም ያላቸው እና ታታሪ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ ባህሪ እና ስነ ምግባር ለመወሰን ፡-

8.2.1.1. ዳይሬክተሩ በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች ቦታዎች እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ታሪክ የሌለው መሆን አለበት፤

8.2.1.2. ዳይሬክተሩ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማሳደር የሚችልበት ወይንም የሚቆጣጠረው ድርጅት ስልጣን ባለው ተቆጣጣሪ የመንግስት አካል የጠየቀውን መረጃ ከደበቀ፣ የተሳሳተ የፋይናንስ ወይም ሌሎች መግለጫዎች ካቀረበ ወይም የተቆጣጣሪ የመንግስት ባለስልጣን መስሪያ ቤት የጠየቀውን የእርምት እርምጃዎች ካላከበረ ወይም የሚጠየቀውን መመሪያዎች ወይም መስፈርቶችን ሳያሟላ የቀረበት አጋጣሚ የሌለው እና

8.2.1.3. ማንኛውም ዳይሬክተር ተጽዕኖ ማሳደር የሚችልበት ድርጅት በፍርድ ቤት ወይም አስተዳደራዊ የዳኝነት ሥልጣን ባለው አካል ወይም በመንግስት ተቆጣጣሪ አካላት ወይም በባለሙያዎች ተቋም እምነት በመጣስ ጉዳዮች ላይ ተመርምሮ፣ ታግዶ ወይም ተቀጥቶ የማያውቅ እና ሌሎች ተዛማጅ የፋይናንስ ወንጀሎች ላይ ተሳትፎ የሌለው መሆን አለበት።

## 8.3. የፋይናንስ ጤናማነት

8.3.1. የቦርድ አባል ሆነው የሚመረጡ ዳይሬክተሮች በገንዘብ ረገድ ጤናማ መሆን አለባቸው፤ የዳይሬክተሮችን የፋይናንስ ጤናማነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን መስፈርቶች ግምት ውስጥ ይገባሉ፡-

8.3.1.1. ዳይሬክተሩ በዳይሬክተርነት ወይም ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ የባለቤት ድርሻ የያዘበት ድርጅት የኪሳራ ክስ ያልተመሰረተበት ወይም ያልከሰረ፤ በኢትዮጵያም ሆነ በሌላ ቦታ ወይም የእሱ ወይም የኩባንያው ንብረቶች በሞግዚት አስተዳዳሪ ያልተያዙበት ወይም ብድር ባለመክፈሉ ምክንያት በኪሳራ ወይም በባንክ ያልታገደበት መሆኑ፤

8.3.1.2. ዳይሬክተሩ በዳይሬክተርነት ወይም ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ባለቤት የሆነበት ድርጅት የባንክ ወይም የሌላ ብድር ግዴታውን ወይም የታክስ ክፍያውን ሳይከፍል ያልቀረ፤

8.3.1.3. ዳይሬክተሩ በዳይሬክተርነት ወይም ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ባለቤት የሆነበት ድርጅት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ባለፉት ሁለት (2) ዓመታት ውስጥ ከማንኛውም የፋይናንስ ተቋም የተበላሸ የብድር ታሪክ የሌለው ፤

8.3.1.4. ዳይሬክተሩ አግባብነት ባለው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት በቂ ስንቅ ሳይኖረው ቼክ በመጻፉ በማንኛውም ባንክ ሂሳቡ ያልተዘጋበት።

## 8.4. ከጥቅም ግጭት ነፃ መሆን እና የመወሰን ነጻነት

8.4.1. ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሚጠቆሙ እጩዎች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ከጥቅም ግጭቶች ነፃ በመሆን በገለልተኝነት እና የአመለካከት ነፃነት በተሞላበት መንፈስ መስራት አለባቸው። በዚሁ መሰረትም፡-

8.4.1.1. ከባንኩ ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚ መኮንኖች እና/ወይም በባንኩ ዋና ዋና የስራ ክፍሎች ላይ በተቀመጡ ሌሎች ግለሰቦች፣ ከማንኛውም የባንኩ

ተፅዕኖ ፈጣሪ ባለአክስዮኖች ወይም ከደንበኞች ወይም ከባንኩ አቅራቢዎች ወይም ተወዳዳሪዎች ጋር ማንኛውም ቤተሰባዊ ወይም የስራ፣ የሙያ፣ የንግድ ዝምድና የሌላቸው፤

8.4.1.2. በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በባንኩ ላይ በሚኖሩ ማናቸውም መደበኛ ፍርድ ቤት ወይም ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጪ ክርክሮች ውስጥ ተሳትፎ የሌለው፤

8.4.1.3. ባለፉት ሁለት (2) አመታት ውስጥ ከባንኩ፣ ከእህት ኩባንያ ወይም ከተቀጽላ ማህበር ወይም ከባንኩ ደንበኞች፣ አቅራቢዎች ወይም ተወዳዳሪዎች ወይም ሌሎች ተቀጽላ ድርጅቶች ጋር የንግድ ወይም የሙያ ወይም የግብይት ግንኙነት የሌለው፣ እና

8.4.1.4. ሌሎች ኢትዮጵያ በብሔራዊ ባንክ የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚያሟላ

### 8.5. ጊዜ የመስጠት ቁርጠኝነት

ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሚመረጡ ግለሰቦች በባንኩ ውስጥ የሚጠበቅበትን ኃላፊነቶች ለማከናወን በቂ ጊዜ ለመስጠት የሚችሉ መሆን አለባቸው።

8.6. የባንኩ ገለልተኛ ዳይሬክተር ሆኖ ለመመረጥ ከላይ በአንቀጽ 8(2)-8(5) የተቀመጡትን ሊያሟሉ ይገባል።

## ክፍል አራት

## የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ማቋቋም፣ አባልነት፣ መመዘኛ እና ስብጥር

### 9. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ ማቋቋም፣

9.1. የቦርድ አባላትን ለመምረጥ በተጠራው የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ የቦርድ ምልመላና አስመራጭ ጊዜያዊ ኮሚቴን ማቋቋም የመጀመሪያ አጀንዳ እንዲሆን በማድረግ ኮሚቴው በጠቅላላ ጉባኤው እንዲቋቋም ይደረጋል፡

9.2. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ 5 (አምስት) አባላት ይኖሩታል።

9.3. ጠቅላላ ጉባዔው 10 (አስር) እጩ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ይጠቁማል። ባገኙት ድምፅ መሠረት አምስቱን የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ያደርጋል።

9.4. ጠቅላላ ጉባዔው የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት በሚስጥር ድምፅ መስጫ ሥርዓት እንዲመረጡ ያደርጋል።

### 10. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባልነት መመዘኛ እና ስብጥር

10.1. የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ለመሆን፦

(ሀ) ባለአክሲዮን መሆን፣

(ለ) የኮሚቴው አባል ሆኖ ለመሥራት ፈቃደኛ መሆን፣

(ሐ) ሠራተኛ ያለመሆን፣

(መ) ቢያንስ አጠቃላይ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኙን ያጠናቀቀ መሆን፡

(ሠ) ህዝብን ከአጭበርባሪነት ወይም ማታለል ለመከላከል በተደነገገ ማናቸውም የኢትዮጵያ ወይም የሌላ ሀገር ህግ መሰረት ጥፋተኛ የሚያስብል ድርጊቶች ስለመፈጸሙ የሚያሳይ ፍርድ ያልተመዘገበበት ወይም ይህ ፍርድ ስለመኖሩ ማስረጃ ያልቀረበበት መሆን ይኖርበታል፡፡

10.2. ከተጠቆሙት ኮሚቴዎቸ መካከል ከፍተኛ ድምጽ ያገኘውን አባል ሊቀ-መንበር እና ሁለተኛ ከፍተኛ ድምጽ ያገኘው ጸሀፊ ሆነው ያገለግላሉ፡

10.3. ጠቅላላ ጉባዔው የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ቁጥር የትኛውንም ቢሆን፣ ከአባላቱ ውስጥ ቢያንስ 2 (ሁለቱ) ተጽዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፣

10.4. በስራ ላይ ያለ የቦርድ ዳይሬክተር የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባል ሆኖ ሊመረጥ አይችልም፣

## ክፍል አምስት

## የእጩዎች ጥቆማ እና የምልመላ ሂደት

### 11.እጩዎችን በምድብ ማስቀመጥ

የቦርድ ምልመላና አስመራጭ ጊዜያዊ ኮሚቴ(ኮሚቴው) ከዚህ በታች በተገለጸው መንገድ በሦስት ምድብ እጩዎች፣ ያስጠቁማል፣ ይመለምላል፡፡

11.1. ምድብ አንድ ላይ ከቦርዱ አጠቃላይ መቀመጫዎች ውስጥ 1/3ኛ (አንድ ሶስተኛ) የሚሆነውን ተጽዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክስዮኖች ብቻ የሚጠቆሙና የሚመረጡ፤

11.2. ምድብ ሁለት ላይ ከቦርዱ አጠቃላይ መቀመጫዎች ውስጥ 1/3ኛ (አንድ ሶስተኛ) የሚሆነውን በሁሉም ባለአክስዮኖች የሚጠቆሙና የሚመረጡ፤

11.3. ምድብ ሶስት ከጠቅላላው የቦርድ አባላት መቀመጫዎች ውስጥ 1/3ኛ የሚሆኑት በዳይሬክተሮች ቦርድ የተመለመሉ እና ለኮሚቴው የተላለፉ እና በሁለም ባለአክሲዮኖች የሚመረጡ ሊሆኑ ይገባል፡፡

11.4. ተጽዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮኖች በማይኖሩበት ጊዜ ኮሜቴው ከላይ ከተዘረዘሩት ምድቦች ውስጥ ምድብ ሁለት እና ሶስት ላይ በተገለጸው ሁኔታ እጩዎችን ይመለምላል፡፡

## 12.የእጩዎች ብዛት፣

ኮሚቴው በእያንዳንዱ ምደብ ለሚኖሩ ዳይሬክተሮች 2 (ሁለት) ዕጥፍ የሚሆኑ ጥቆማዎች ተቀብሎ የተጠቆሙትን በእጩነት ይመለምላል፡፡ ከተጠቆሙት ዕጩዎች ቢያንስ አራት ሴቶችን ይመለምላል፡ ፡

## 13.የጥቆማ አቀባበል፡

13.1. ኮሜቴው ከላይ ምድብ ሶስት ተብሎ ከተቀመጠው ውጭ ለእያንዳንዱ ምድብ ከዚህ በታች በተገለጸው መንገድ የእጩዎች ጥቆማ ይቀበላል፡-

13.1.1. በጠቅላላ ጉባኤው ላይ የተገኘ ባለአክሲዮን እጅ በማወጣት በኮሚቴው ዕድሉ ሲሰጠው ራሱን ወይም ሌላ ባለአክሲዮን ወይም የባንኩን ሠራተኛ መጠቆም ይችላል፡፡

**13.1.2.** ጠቋሚው ባለአክሲዮን የተጠቋሚውን ሥም፣ የትምህርት ደረጃ፣ የስራ ልምድ እንዲሁም ባህሪ መግለጽ እና ይህን ሁኔታ ከዚህ መመሪያ ጋር ከተያያዘው የማረጋገጫ ፎርም ላይ በመዘርዘር እውነት መሆኑን እና ሀሰት ሆኖ ቢገኝ ሀላፊነት ለመውሰድ የተስማማ መሆኑን በፊርማ በማረጋገጥ መስጠት አለበት፡፡

13.1.3. የሚጠቆመው እጩ የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ከሆነ ድርጅቱን በመወከል በቦርድ አባልነት የሚያገለግለው ሰው ማንነት፣ የትምህርት ደረጃ፣ እና ስራ ልምድ አብሮ እንዲገለጽ ኮሚቴው ያደርጋል፡፡ በዕለቱ ይህንን ማረጋገጥ ካልተቻለ ድርጅቱ በቀጣይ እንዲያሟላ ይደረጋል፡፡

13.1.4. ኮሚቴው በጥቆማ ጊዜ በሚከተሉት የሙያ ዘርፎች የትምህርት ዝግጅት እና ተጨባጭ ልምድ ያላቸው በእያንዳንዱ ዘርፍ ሁለት ግለሰቦች እንዲጠቆሙ ጥረት ያደርጋል፡፡ በአንደኛው ዘርፍ ላይ ሁለት ሰዎች ተጠቁመው ከሆነ በሌሎች ዘርፎች ላይ ግለሰብ ለሚጠቆሙ ባለአክሲዮኖች ቅድሚያ ዕድል ሊሰጥ ይገባል፡፡ የሙያ የዘርፎች ዝርዝር፡- በንግድ ስራ አመራር፤ በባንክ እና/ወይም በፋይናንስ፣ በአካውንቲንግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ፣ በንግድ አስተዳደር፣ በኦዲቲንግ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኢንቨስትመንት አስተዳደር ናቸው፡፡

13.1.5. የጥቆማ ሂደቱ በምደብ 1 እና 2 ላይ የተጠቀሱት ቁጥሮች ላይ በእያንዳንዱ ምድብ ሁለት ዕጥፍ ቁጥር እስኪገኝ ድረስ መቀጠል አለበት፡፡

## 14. እጩዎችን መመልመል

14.1. ኮሚቴው ከላይ አንቀጽ 13 መሰረት ጥቆማ ከተቀበለ በኂላ ተጠቋሚዎቹ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 እና በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ላይ የተቀመጡ መመዘኛዎች የሚያሟሉ መሆናቸውን ካረጋገጠ እና ቢመረጡ ለማገልገል ፈቃደኛ መሆናቸውን እና ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን

ማረጋገጫ የፈረሙ መሆኑን ካረጋገጠ በኂላ የተጠቆሙትን ዕጩ አድርጎ በየምድቡ ይመለምላል፡
፡

14.2. ከላይ የተጠቀሰውን የማያሟሉ ሆነው ባገኛቸው ግለሰቦች ምትክ ደግሞ ከላይ አንቀጽ 13 ላይ በተገለጸው መሰረት ጥቆማ ከተቀበለ በኂላ እንደገና በአንቀጽ 14.1. መሰረት ይመለምላል፡፡

## 15. የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ምልመላ ሂደት

በምድብ ሶስት የተቀመጡትን ገለልተኛ ዳይሬክተሮች የሚመለመሉበትን ሥርዓት ቦርዱ ያወጣል፡፡ በዚያ ሥርዐት መሰረት የተመለመሉ ገለልተኛ ዳይሬክተሮችን ስም፣ የትምህርት ደረጃ፣ ልምድ፣ የገለልተኛነት ማረጋገጫ እና ሌሎች መረጃዎችን በማካተት ለኮሚቴው ያስተላልፋል፡፡

# <u>ክፍል ስድስት</u>
# <u>የምርጫ አፈጻጸም</u>

### 16.እጩዎችን ማሳወቅ እና የድምጽ አሰጣጥን መግለጽ

16.1 ኮሚቴው ከላይ በተጠቀሰው መንገድ የተጠቆሙ እና የተመለመሉ እጩዎችን በአንቀጽ 11 በተቀመጠው መሰረት ለሶስት ወይም ሁለት ምድብ አድርጎ የእጩዎችን ስም፣ እድሜ፣ የትምህርት ሁኔታና ልምድ ለጠቅላላ ጉባኤው ይገልጻል ፡፡

16.2 ኮሚቴው የተመለመሉት እጩዎች ራሳቸውን በ 02 ደቂቃ ውስጥ እንዲገልጹ እድል ይሰጣል፡
፡

16.3 ኮሚቴው ለጉባኤ ተሳታፊዎች የተመለመሉት እጩዎችን በተመለመሉበት ምድብ ውስጥ ብቻ መመረጥ የሚችሉ መሆኑን እና ከእጩዎቹ መካከል የሚመርጧቸውን የድምጽ ካርድ መስጫ ላይ መጻፍ እንዳለባቸው እና ተያያዥ ነገሮችን ማስረዳት አለበት፡፡

### 17.የድምጽ መስጫ ካርድ፣

17.1 ቦርዱ ከሚመለከተው የባንኩ የሥራ ክፍል ጋር በመተባበር ባለአክሲዮኖች የሚመርጡበትን የሚስጥር ድምፅ መስጫ ካርድና ሳጥኖች ያዘጋጃል፡፡ የሚስጥር ድምፅ መስጫው ካርድ ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

ሀ. የባለአክሲዮኑን ስም፣

ለ. ባለአክሲዮኑ ያለውን የተፈረመ የአክሲዮን መጠን/ብዛት፣

ሐ. የስብሰባ ተካፋይነት ልዩ መታወቂያ ቁጥር፣

መ. የባንኩን ስምና አርማ፣

ሰ. የባንኩን ማኅተም፣

ረ. ባለአክሲዮኑ የሚመርጣቸውን እጩዎች የሚጽፍበት ባዶ ቦታ፣

17.2 ባለአክሲዮኑ በጉባዔው ስለመገኘቱ በሚፈርምበት ጊዜ የሚስጥር ድምፅ መስጫ ካርዱን ይረከባል፡

## 18. የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት፣

18.1 ባለአክሲዮኖቹ ለድምፅ መስጫ የተዘጋጀውን ካርድ በመጠቀም በእያንዳንዱ ምድብ ስር ለተጠቆሙት እጩዎች እንደሚከተለው ድምጽ ይሰጣሉ ፡-

18.1.1 በምድብ አንድ ስር ለቀረቡ እጩዎች ድምፅ መስጠት የሚችሉት ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ ናቸው፡፡

18.1.2 በምድብ ሁለት እና ሶስት ስር ለቀረቡ እጩዎች ሁሉም ባለአክሲዮኖች ድምፅ መስጠት ይችላሉ፡

18.2 ባለአክሲዮኖች በድምፅ መስጫ ካርዱ ላይ የሚመርጡትን እጩ/እጩዎች ስም ለዚሁ ተግባር በተሰጠው ቦታ ከፃፉና ከፈረሙበት በኂላ የድምፅ መስጫ ካርዱን ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ያስገባሉ፡፡

18.3 የድምፅ መስጫ ካርዱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግድፈቶች ከተገኙበት ውድቅ ይደረጋል፣

**ሀ**) የባለአክሲዮኑ ስም የሌለው ከሆነ፣

**ለ**) የባለአክሲዮኑን የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት(ድምጽ) የማያመለክት ከሆነ

**ሐ**) የባንኩ ስም እና አርማ ያልታተመበት ከሆነ፣ እንዲሁም

**መ**) የዕጩ ተመራጩ ስም ወይም ለምርጫው ተብሎ ለእጩው የተሰጠ መለያ ቁጥር ያልተፃፈበት ከሆነ፣ እንዲሁም

**ሠ**) የመራጩ ፊርማ የሌለበት ከሆነ፣

19. **የምርጫውን ውጤት ስለመግለጽ**

19.1. ኮሚቴው የድምፅ ቆጠራው እንደተጠናቀቀ የድምፅ አሰጣጡ እና የቆጠራ ሂደቱ እንዲሁም የምርጫው ውጤት ትክክለኛ ስለመሆኑ ለዚሁ በተዘጋጀ ፎርም ላይ በመፈራረም ማረጋገጥ አለበት፡፡

19.2. ኮሚቴው የድምፅ ቆጠራውን ውጤት ድምፅ በተሰጠበት ቀን ለጠቅላላ ጉባኤው ይገልፃል፡፡ ይህ የማይቻል ከሆነ ግን በቀጣዩ የሥራ ቀን በባንኩ ድረ-ገጽ ላይ በማውጣት እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡

19.3. በምርጫው በእያንዳንዱ ምድብ ከፍተኛ ድምፅ ያገኙ እጩዎች በቦርድ አባልነት ይመረጣሉ፡፡

19.4. በምርጫው የተወዳደሩ ሴት እጩዎች በቦርድ አባልነት ለመመረጥ የሚያስችል ድምፅ ያላገኙ እንደሆነ የሴቶችን የፆታ ተዋፅኦ ለመጠበቅ ሲባል በእጩነት ከቀረቡ ሴቶች መካከል ሁለቱ ባገኙት ድምፅ መሠረት በሽግሽግ በቦርድ አባልነት እንዲሾሙ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን በየትኛውም ምድብ ውስጥ እጩ ሆነው ከቀረቡ ሴቶች መካከል አንዲት ሴት ባገኘችው ከፍተኛ ድምፅ መሠረት በቀጥታ በቦርድ አባልነት የተመረጠች እንደሆነ በሽግሽግ የመሾም መብቱ ተፈፃሚ የሚሆነው ለአንዲት እጩ ሴት ብቻ ይሆናል፡፡

19.5. ያልተመረጡ ዕጩዎች በምርጫው ባገኙት ድምፅ መሠረት በተጠባባቂነት ይያዛሉ፡፡

20. **የምርጫ ሰነዶችን ስለመያዝ**

20.1. ኮሚቴው ለእያንዳንዱ እጩ ድምፅ የተሰጠበት የምርጫ ካርድ ለብቻ እንዲያዝ ያደርጋል፣ ለዚህም ምርጫው እንደተጠናቀቀ ካርዶቹን ለማህበሩ ፀሐፊ ያስረክባል፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

21. **የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት፣**

ይህን መመሪያ ተግባራዊ ሲደረግ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎችና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

22. **መመሪያውን ስለማሻሻል፣**

ይህን መመሪያ በጠቅላላ ጉባዔው በማፀደቅ ማሻሻል ይቻላል፡፡ ማሻሻያው ግን ከብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ጋር መቃረን የለበትም፡፡

23. **የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች**

23.1. ታህሳስ 2012 ዓ.ም የወጣው **"የዘመን ባንክ አ.ማ የዳሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ መመሪያ(2012)"** በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

23.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምልመላ እና የምርጫ አሠራርን በሚመለከት ማንኛቸውም ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ የባንኩ የውስጥ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ላይ በተደነገጉት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 24. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ፣

የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ-ጉባኤ በብሔራዊ ባንክ እና በሚመለከታቸው የመንግስት አካል መጽደቅ እና መመዝገብ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ በጠቅላላ ጉባዔው ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## የማረጋገጫ ቅጽ

( በጠቋሚ የሚሞላ)

የጠቋሚው ሙሉ ስም------------------------------------------የአክሲዮን መለያ ቁጥር -----------------

የሚጠቆመው ሙሉ ስም -----------------------------------------

የትምህርት ደረጃ እና ዘርፍ ፡ ምሳሌ ቤኤ በአካውንቲንግ

**ሰርተፍኬት፡**

**የስራ ልምድ፡**

**ዕድሜ፡**

**ባህሪ እና ሥነ-ምግባር፡**

ከላይ የተሰጠው መረጃ ትክክል ስለመሆኑ አረጋግጣለሁ፣ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ ሀላፊነት እወስዳለሁ፣ለምሳሌ ባንኩ ሌላ ጉባኤ ማድረግ ቢያስፈልገው የባንኩን ወጪዎችን ለመሸፈን ቃል ገብቻለሁ።

የጠቋሚው ሥም------------------------------ ፊርማ----------------------- ቀን --------------------

ተጠቋሚ የሰጠው ማረጋገጫ

እኔ ……………………………………………ከላይ የተሰጠው መረጃ ትክክል ስለመሆኑ አረጋግጣለሁ፣ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ ሀላፊነት እወስዳለሁ፣ለምሳሌ በተሳሳተው መረጃ ምክንያት ባንኩ ሌላ ጉባኤ ማድረግ ቢያስፈልገው የባንኩን ወጪዎችን መሸፈን ቃል ገብቻለሁ። እንዲሁም የቦርድ አባል ለመሆን ፈቃደኛ መሆኔን እየገለጽኩ በአሁኑ ሠአት የጥቅም ግጭት የሚያሥከትል ፣ የመወሰን ነጻነትን የሚገፉ ወይም ሀላፊነቴን እንዳልወጣ የሚያደርግ የጊዜ ጥበት ሁኔታ ውስጥ ያልሆንኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

የተጠቋሚው ሥም---------------------------------- ፊርማ-------------------------- ቀን--------------